## ኦክቶበር 2017 QuickNotes ቁ.2

**ለ2017 በት/ቤቶች በተቋቋሙ የፍሉ ክትባት ክሊኒኮች ተመዝገቡ!**

የ2017 የፍሉ ወራት አሁን ተቃርቧል። ጤናማ ለመሆንና ፍሉን ለመከላከል እናንተና ልጆቻችሁ ለማድረግ የምትችሏቸው ቀላል እርምጃዎች አሉ። እነርሱም በየአመቱ የፍሉ ክትባት መውሰድን ያካትታሉ።

የሞንጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምርያ (Montgomery County Department of Health and Human Services) ኖቬምበር 9 ከ1:30 ፒ.ኤም እስከ 4:30 ፒ.ኤም ለ18 ዓመት እና ከዚያ በታች እድሜ ለሆኑ ልጆች በJohn F. Kennedy፣ በNorthwest፣ እና በRockville ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመርፌ የሚወጋ የፍሉ ክትባት በነፃ ይሰጣል። እንዚህ ክሊኒኮች ለማንኛውም የትምህርት እድሜ ለደረሰ ልጅ ክፍት ይሆናሉ።

ክሊኒኮቹ ነፃ ናቸው፤ ነገር ግን በክትባት አቅርቦት እጥረት ምክንያት ምዝገባ ያስፈልጋል። ለተጨማሪ መረጃ፡- የMontgomery County የጤና እና የሰብአዊ አገልገሎቶች መምርያ ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

የፍሉ እና ሌሎችም ወቅታዊ በሽታዎች እንዳይሰራጩ ለመከላከል እርስዎና ቤተሰብዎ ልትወስዷቸው የምትችሉት ተጨማሪ እርምጃዎች እነዚህ ናቸው፡-

1. በተለይም ካሳላችሁ ወይም ካስነጠሳችሁ በኋላ እጆቻችሁን ዘወትር በሳሙናና በውሃ ታጠቡ፣ ወይም በአልኮል የተነከረ/የረጠበ የእጅ መጥረጊያ ተጠቀሙ። በMCPS-የተፈቀደ ጀርም መከላከያ መያዣዎች (hand sanitizer dispensers) በየት/ቤቶቹ በተለያዩ ቦታዎች (ለምሳሌ፡- በካፊቴሪያ አጠገብ፣ ወይም ሁለገብ-አገልግሎት የሚካሄድበት ክፍል፣ በዋናው ፅ/ቤት አጠገብ) ይገኛሉ፡፡

2. ሲያስላችሁ ወይም ሲያስነጥሳችሁ፣ አፍንጫችሁንና አፋችሁን በእጅጌ ወይም በቲሹ ሸፍኑ እና ቲሹውን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጣሉት።
3. የጀርም/የተላላፊ በሽታ ብክለት ለመቀነስ አይኖቻችሁን፣አፍንጫ ወይም አፋችሁን ከመንካት ተቆጠቡ።
4. ትኩሳት፣ሳል፣ማስነጠስ፣ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ/ንፍጥ፣የራስ ምታት እና የአካል ህመም የመሳሰሉ ምልክቶች ከተሰማዎት ከስራ ወይም ከት/ቤት ቀርቶ ቤት መዋል።
5. ስለ ልጆቻችሁ ጤና ቅሬታ ካላችሁ፣እባካችሁ ሀኪምዎን በአስችኳይ ያግኙ፣ወይም አጣዳፊ ከሆነ፣ 911 ይደውሉ።

ተጨማሪ የፍሉ መከላከያ መረጃዎች በሚከተሉት ድረ-ገጾች ይገኛሉ፡-

MCPS http://www.montgomeryschoolsmd.org/emergency/flu/index.aspx/
Centers for Disease Control (የበሽታ መቆጣጠርያ ማዕከሎች)
http://www.cdc.gov/flu/protect/preventing.htm
Montgomery County http://www.montgomerycountymd.gov/resident/flu.html

**በቦርድ ስብሰባዎች የህዝብ አስተያየት ምዝገባ ሂደት ለውጥ እየተደረገ ነው**

የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (Montgomery County Board of Education) የሥራ ስብሰባዎች ላይ ለመናገር የመመዝገቢያ ስልቱ ተቀይሯል።

ከማህበረሰቡ በተሰጡ አስተያየቶች እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት፣ በድረ-ገጹ ላይ የሚገኘውን "Google form" በመጠቀም ለመናገር እንዲመዘገቡ ቦርዱ ህብረተሰቡን እየጠየቀ ነው ግለሰቦች ሰኞ ጠዋት የቦርድ ስብሰባ ከመጀመሩ አስቀድመው ቢሮ ከመደወል ይልቅ የGoogle formዓርብ ጠዋት ጀምሮ እስከ ሚቀጥለው ሰኞ የቦርድ የሥራ ስብሰባ እኩለ ቀን ድረስ ለመጠቀም ክፍት ይሆናል **በዚህ አዲስ ሂደት፣ ከአሁን ወድያ የስልክ ጥሪዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።**

የቦርድ ውሳኔዎችን በሚመለከት የማህበረሰቡ አስተያየትና ምላሽ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ቦርዱ ከማህበረሰቡ አባላት የሚሰጡትን አመለካከቶችና አስተያየቶች ማዳመጥ/መስማት ወሳኝነት አለው ወደ መስመር ላይ ቅርፀት በመቀየሩ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተጨማሪ ግለሰቦችን ለመድረስና ለመስማት እንደሚቻል የቦርዱ እምነት ነው።

ጥያቄዎችን ወደ ቦርዱ የህግ ረዳት፣ Patricia Swanson/ፓትሪሻ ስዋንሰን፣ መምራት ይቻላል።
Patricia_R_Swanson@mcpsmd.org

**ስለ ስራና የቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች በThomas Edison ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለፎል በተዘጋጀ የፕሮግራም ቀን/Open House ተገኝተው ይማሩ!**

የMCPS ወላጆችና ተማሪዎች በቶማስ ኤድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Thomas Edison High School of Technology) የፎል ዝግጅት በሚቀርብበት ቀን ሀሙስ፡ ኦክቶበር. 26 ከ5 p.m. እስከ 8 p.m. እንዲገኙ ተጋብዘዋል። በMCPS የሚገኙ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በEdison's 17 የስራና የቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች በአንዱ ለመመዝገብ የማመልከት አማራጭ አላቸው። ተማሪዎች በEdison በየቀኑ ሶስት የትምህርት ክፍለ ጊዜ በመከታተል በእያንዳንዱ ሰሚስተር 1.5 ክሬዲቶችን ያገኛሉ። ዋጋ ያላቸው ሙያዊ የምስክር ወረቀቶችና ላይሰንሶች/የስራ ፈቃዶች ከመስጠት ባሻገር፣ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲትም ማግኘት ይችላሉ። በክፍት አዳራሽ፣ መምህራን፣ተማሪዎች፣ የቢዚነስና የኢንዱስትሪ ሽሪኮች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና በፕሮግራሞች ለቀረቡ ስራዎች ማብራርያ ለመስጠት በስፍራው ይገኛሉ። Edison የሚገኘው በ12501 Dalewood Drive, Silver Spring ነው። [የት/ቤቱን መገናኛ አውታር ይጎብኙ!]

**አገራዊ የሂስፓኒክ ኮሌጅ ትርኢት ቀን ኖቬምበር 7 ይደረጋል። (National Hispanic College Fair Set for Nov. 7)**

The National Hispanic College Fair/አገራዊ የሂስፓኒክ ኮሌጅ በአል (NHCF) ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 7, 2017 በጌትስበርግ ቦህረር መናፈሻ ቦታ የማህበረሰብ ማዕከል(Bohrer Park Community Center in Gaithersburg) ይካሄዳል። ይህ አመታዊው አገራዊ የሂስፓኒክ ኮሌጅ ፌር (NHCF) እና በ(MCPS) የተደገፈ ዝግጅት ለጁኒየሮች እና ለሲንየር ተማሪዎች ነፃ ነው። ዝግጅቱ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች ሰፊ መዳረሻና እድል ለመስጠት ውዴታ የገቡ ከ50 የሚበልጡ ኮሌጆች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ይቀርባሉ። በዚህ አመት አዲስ የሚከሰት ሁኔታ የAchieving Collegiate Excellence and Success/በኮሌጅ ልቀትንና ስኬትን ማግኘት (ACES) አሰልጣኞችና የMCPS የቀድሞ ተማሪዎችን ያቀፈ ለኮሌጅ ዝግጁነት እና ስለ ሥራ መረጃ የሚሰጥ ጓድ ያካትታል።

የMCPS ተማሪዎች የሚሳተፉት ትምህርታቸውን በመከታተል ነው፤ ይህ ክውነት ለህዝብ ክፍት አይደለም የሚካሄደውም በትምህርት ቀን ነው። ለዚህ ዝግጅት መመዝገቢያና ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ/ፎርም ልጅዎ በሚ(ምት)ማርበት ት/ቤት የኮሌጅ እና የሥራ አስተባባሪ ዘንድ ይገኛል።

ስለ ኮሌጅ እና ስራ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በነፃ ለሕዝብ ክፍት ከሚደረጉት ዝግጅቶች በቅድሚያ ሁለት የተቀናበረ ዝግጅት ይኖራል። ሁለቱም ዝግጅቶች የሚካሄዱት በስፓኒሽ እና በእንግሊዝኛ ነው።

- እሁድ ኦክቶበር 22 በዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሚዲያ ማዕከል (Watkins Mill High School Media Center) ከ11:30 a.m. – 2:30 p.m.

- ሐሙስ ኦክቶበር 26 በኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚዲያ ማዕከል እና በካፌቴርያ (Kennedy High School Media Center and Cafeteria) ከ6-9 p.m.

ለተጨማሪ መረጃ፣ የNHCF አስተባባሪ Patty Maloney/ፓቲ ሜሎኒይ በPatricia_A_Maloney@mcpsmd.org ወይም በ301 353-8029 ተገናኙ።

**የሞንጎመሪ ኮሌጅ (Montgomery College) የወደፊትና ወቅታዊ የኮሌጅ ተማሪዎችን FAFSAን እንዲሞሉ ለማገዝ በልዩ ዝግጅት ያስተናግዳል!**

የ2018-2019 Free Application for Federal Student Aid/ለፌደራል የተማሪ እርዳታ (FAFSA) ነፃ ማመልከቻ የመጣው ኦክቶበር 1, 2017 ነው። ኮሌጅ የሚገቡ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው FAFSA ፎርም ለመሙላት በሁለተኛው አመታዊ FAFSA Fever/በሚጋጋልበት ወቅት ፎርሙን ለመሙላት ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት ይችላሉ። ይህ ድርጊት የሚከናወነው በሞንጎመሪ ኮሌጅ የተማሪ ፋይናንስ ድጋፍ ቢሮ ቅዳሜ ኦክቶበር 28 ከ12–3 p.m፣ በጀርመንታዎን የሚገኘው ሞንጎመሪ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ Bioscience Education Center 20200 Observation Drive አድራሻ ላይ ነው።

FAFSA Fever ቤተሰቦችን FAFSAን—ለስኮላርሺፖች፣ የገንዘብ ስጦታዎችና ብድሮች ለማግኘት ብቃት ለማግኘት በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተፈላጊ ፎርም—ሲሞሉ የሚያግዛቸው ክውነት ነው። FAFSA በሚጋጋልበት ወቅት በነፃ ለህዝቡ ክፍት ነው። በዚህ ወቅት የኮሌጅ ተማሪ የሆኑና FAFSA ለማሳደስ የሚፈልጉ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚጠይቁ በዚህ ዝግጅት መሳተፍ ይችላሉ።

ተማሪዎች እና ወላጆች FAFSA በኢንተርኔት/online በሚሞሉበት ጊዜ የፋይናንስ እርዳታ ባለሞያዎችን ለማግኘትና ለማነጋገር እድል ይኖራቸዋል። እንዲሁም የሞንጎመሪ ኮሌጅ ኮምፒውተር ላብ ለመጠቀም ይችላሉ። በዚህ ወቅት የሞንጎመሪ ኮሌጅ ተማሪዎች የሆኑ $250 ስኮላርሽፕ ለማሸነፍ መግባት ይችላሉ።

የ23 አመት ወይም ከዚያ በታች እድሜ ያላቸው ተማሪዎች FAFSA ግለትን ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ጋር መከታተል አለባቸው። የቦታ ውስንነት ስላለ መመዝገብ አስፈላጊ ነው። ለመመዝገብና ማምጣት ያለባችሁን ሰነዶች ሙሉ ዝርዝር ለማውረድ፣ እባካችሁ www.montgomerycollege.edu/FAFSAFever ጎብኙ። Please visit www.montgomerycollege.edu/FAFSAFever to register and download a complete list of documents to bring.